# <u>ጣጣዋ የማያልቀው የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን</u>

# <u>ክፍል ፩</u>

## <u>ማሳሰቢያ</u>

**በለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተከሰተውን ችግር አስመልክቶ በተለያዩ ድኅረ ገጾች ፣ በዩቲዩብ ፣ በኢሳት ቲቪ የተካሄዱትን ውይይቶች እንደተከታተላችሁ አምናለሁ። እኔም ይህ ሁሉ ነገር ከቁጥጥር ውጭ ከመውጣቱ በፊት የታዘብኩትን አይቼ አስቀድሜ ችግሩን ከነ መፍትሔ ሐሳቡ በተከታታይ ጽሑፎች ማቅረቤ ይታወቃል።** http://ethiopianorthodox.org/amharic/miscellenous/london.html

**ይሁን እንጂ የተሰነዘረውን ሐሳብ አይቶና መርምሮ መፍትሔ ከማምጣት ይልቅ ፤ ሁሉን ተቆጣጥረነዋል ማንም አያሸንፈንም በማለት በወቅቱ በአመራር ላይ የነበሩት የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አባላት በእልህ በያዙት ቀጠሉበት። እኔም ሆነን ሌሎች ከሚያዚያ 2003 ዓ.ም እስከ መስከረም 2004 ዓ.ም በተቻለን አቅም ለምዕመናኑ ያለውን እውነታና አደጋውን ለማመልከት በጽሑፍ ሞክረናል።**

http://ethioview.com/LondonMariam.html

**ከዚያ በኋላ ግን ሰሚ ስላልተገኘ ፣ በቤተ ክርስቲያኗ አደባባይ እንካ ሰላምታና ፀብ እየከረረ ስለመጣ ፤ ሁኔታው በራሱ እስኪጠራ ድረስ ምንም ጽሑፍ ከመጻፍ ተቆጥበን መጨረሻውን ማየት መረጥን። ሁላችሁም እንዳያችሁት በዩቲዩብ ላይ ፤ እነዚያ በተለያየ ጊዜ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ሲጮኹ ፣ ሲሳደቡ የነበሩት በእውነት ፈሪሀ እግዚአብሔር አላቸው ወይ ብሎ ያልጠየቀ ሰው ያለ አይመስለኝም። በመጨረሻው አብረው ለለፉት ዓመታት በጥቅም ተሳስረው በአንድነት በቦታው ላይ ሲናኙ የነበሩት የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አባላት ፣ የእነ ሻለቃ ማሞ ለማ እና ጌታቸው በሻውረድ ጀሌዎች እንዲሁም ጥቂት ካህናት ፤ የእነሱ አንሶ ለብዙ ዓመታት አብሮ የኖረውን ሰው እንዲቃቃር አድርገው ፤ በተጨማሪም በለንደን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን "ሥርዓት አልበኛ" የሚል ስም በመላው ዓለም ባሉ ኢትዮጵያውያን ዘንድ አሰጥተው ፤ ቤተ ክርስቲያኗን ዘግተው ሕዝቡን በትነዋል። በመጋቢት 1 ቀን 2005 ዓ.ም የተዘጋችው የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያንም ፤ በዓመቱ ታህሳስ 2006 ዓ.ም ተከፍታ አገልግሎት መስጠት ጀምራለች። በአሁኑ ወቅት ሕጋዊ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ስለሌለ ፤ አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ ጥረት እየተደረገ ነው። ይህ እርምጃ አስፈላጊ ቢሆንም ፤ አሠራሩ ላይ ግን ካሁኑ የሚታየው ስህተት ቤተ ክርስቲያኗን እንደገና ወደ ሌላ የማያልቅ ችግር ውስጥ የሚከት ነው። አንዳንዶች አሁን ቤተ ክርስቲያናችን ተከፍቷል ለምን ሌላ ጽሑፍ ይጻፋል ብለው ቅር ሊላቸው ይችላሉ። <u>ነገር ግን የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ፤ ምርጫው እንዴት መካሄድ እንዳለበት ፣ በምን ሕግ ፣ የሕጉ ጉዳትና ጠቀሜታ ፣ ስለሚመረጡ አባላት የመሳሰሉትን አስቀድሞ ለመጠቆምና ፤ ያለፍናቸው ችግሮች እንዳይደገሙ ከወዲሁ ለማሳሰብ ነው።</u>**

## <u>ሌባ ሲካፈል እንጂ ሲሰርቅ አይጣላም</u>

**በዚህ ጽሑፍ ላይ ድጋሚ ስለተፈጠረው ችግር መጻፍ አልፈልግም። የችግሩን መንሥኤና ሙሉ ዝርዝሩን ማወቅ የሚፈልግ ከላይ ማሳሰቢያው ላይ ያለውን ሊንክ ከፍቶ ማንበብ ይችላል። የሆኖ ሆኖ በቀጥታ ለችግሩ መንሥኤ የሆነው ከዚህ ቀደም ኢሳት ላይ በተደረገውም ውይይትም ይሁን ፤ በሌላ ሚዲያ ላይ ያልተጠቀሰው እንኳር የሆነውን ሁለቱም የተጣሉት ወገኖች ሊያነሱት የማይፈልጉትን ዋናው የችግሩ መንስኤ**

እዚህ ላይ ማስገንዘብ ፈልጋለው። እዚህ ጋ ሁለቱ ወገኖች ስል በመጀመሪያ አንድ ላይ ፈላጭ ቆራጭ ሆነው በኋላ ግን የተጣሉትን ፤ ማለትም ካህናቱን አባረው ለብቻቸው የቀሩት አባ ግርማ ከበደ ፣ መምሬ አባተ ጎበና እና መሪጌታ አለማየሁ እንዲሁም አሁን ደግሞ ከውጭ ሆነው አልሞት ባይ ተጋዳይ የሆኑት የእነ ሻለቃ ማሞ ለማ እና ጌታቸው በሻውረድ እንዲሁም ጀሌዎቻቸው ናቸው።

ጥያቄው እነዚህ እንደ እጅና ጓንት ሆነው አብረው እንዴት ሊዋደዱ ቻሉ? ፍቅራቸውስ ወደ ፍጹም ጠላትነት እንዴት ተለወጠ? - ይህች በአውሮጳ ቀደምትነት ያላት ቤተ ክርስቲያናችን በቆሞስ አባ አረጋዊ በኋላ አቡነ ዮሐንስ በተባሉት ከተመሠረተች ወደ 40 ዓመታት ያስቆጠረች ሲሆን ፤ በእነዚህ ዓመታት ብዙ ፈተና ያሳለፈች ናት። እኝህ አባት በመጀመሪያ የተላኩት ለካረቢያን ወንድሞቻችን ሲሆን ፤ ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ ብዙ ወገኖቻችን እየተሰደዱ ወደዚህ  ሀገር ሲመጡ ወደ ቤተ ክርስቲያኗ መምጣት ጀመሩ። ይሁን እንጂ ውሎ አድሮ በሁለቱ ማህበረሰቦች መካከል አለመግባባት ስለተፈጠረ ሊከፈሉ ችለዋል። ኢትዮጵያውያኑም እንደ አውሮጳውያኑ አቆጣጠር በ1988 ወደ ቤዝ ዎተር በሚገኘው ቅዱስ ማቴዎስ ቤተ ክርስቲያን ትንሽ አዳራሽ ውስጥ እየተሰባሰቡ መደበኛ የዕለተ እሁድ ጸሎታቸውን ቀጠሉ። እየዋለ እያደር በአማካኝ ከ 40 -50 የማይበልጡ ምዕመናን የሚገለገሉባት አዳራሽ በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን ምዕመናን ማስተናገድ ስላልቻለች ፤ ከፍ ያለ ቤተ ክርስቲያን ተፈልጎ ወደ ሜይ ፌር ገባን። ግልጋሎቱ በሰፊው ቀጥሎ ለሥራ አካሄድ እንዲመች ፤ የውስጥ ደንብ እንዲወጣ ሦስት አባላት ያሉት የመጀመሪያውን አርቃቂ ኮሚቴ አቡነ ዮሐንስ አቋቁመው ሳለ በመሐል ዐረፉ። ከእሳቸው ዕረፍት በኋላ ግን ማኅበረ ካህናቱ ከሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ጋር በመመካከር የውስጥ ደንብ አርቃቂ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥራው ቀጠለ። ይሁን እንጂ ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ/አማኑኤል ወደ ለንደን መጥተው ከአንዳንድ ካህናትና ምዕመናን ጋር በመሆን ቤተ ክርስቲያናችን ለመንጠቅ ባደረጉት ሙከራ ወቅት ሥራው ተቋረጠ። አሁን ወደ አለንበት ቅዱስ ፊሊጶስ ቤተ ክርስቲያን (ባተርሲ) ከገባን በኋላ ቀደም ብለው የተፈጠሩ ችግሮችና ፤ እንዲሁም በወቅቱ እየተነሳ ያለውን አለመግባባት በማየት ሁሉም ማኅበረ ካህናትና ምዕመናን የተስማማበት ፤ የውስጠ ደንብ አርቃቂ ኮሚቴ ተቋቁሞ ከዚህ ሀገር ሕግ ጋር የሚሄድ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ተዘጋጅቶ ቤተ ክርስቲያናችን በእሱ እንድትመራ የሚል ነበር። በውሳኔው መሠረት 12 ሰዎች ያካተተ ኮሚቴ ተቋቋሞ ፤ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ  አርቅቆ ሁሉንም አባላት አወያይቶ በመጨረሻም በጠቅላላው መንፈሳዊ ጉባኤ (ማኅበረ ካህናትና ምዕመናን) በሰኔ 1998 ዓ.ም  (June 2006) ጸድቆ አገልግሎት ላይ ለመዋል በቀቷል። ይህ ደንብ በወጣ በዓመቱ በግንቦት 1999 ዓ.ም (May 2007) በአዲሱ የውስጠ ደንብ መሠረት የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ተቋቋሞ ማዕከላዊ አሠራርንን በመዘርጋትና የሕዝብን አመኔታ በማግኘት 1.8 ሚሊየን ፓውንድ በማውጣት ለትውልድ የሚተላለፍ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንን ለመግዛት ተችሏል። የውስጥ ደንቡን ያንብቡ ፤ http://ethiopianorthodox.org/biography/constitution.pdf

ይህን የውስጠ ደንብ ሲሠሩ ከነበሩት አንዱ ሻለቃ ማሞ ለማ የውስጠ ደንቡ ሲረቀቅ ፤ የካህናት ጉባኤ አያስፈልግም በማለት ብዙ የተከራከረ ሲሆን በተደጋጋሚም ጥላቻውን ሲያሳይ የኖረ ነው። ይሁን እንጂ ደንቡ ከወጣ በኋላ ካህናቱ በሕብረት አገልግሎቱን ለማቀላጠፍና ፤ እንዲሁም በመሐከላቸው ችግር ሲፈጠር በቀላሉ እየፈቱ በአንድነት ማገልገል ለመቻላቸው የውስጥ ደንቡ እንደረዳቸው ሁሉም የሚያውቀው ሐቅ ነው።

ነገር ግን ውሎ አድሮ እነ ሻለቃ ማሞ ለማ ለምን የካህናት ጉባኤ እንዳይመሠረት እንደ ፈለጉ መረዳት አያስቸግርም። የሻለቃ ማሞ ለማ እና የጌታቸው በሻውረድ ጀሌዎች ፍራቻ ፤ ካህናት ሕብረት ካላቸው ፤ ቤተ ክርስቲያኗን ወደፊት በቦርድ አድርገው ለመቆጣጠር እንደማይችሉ ስለገባቸው እንዴት ማፍረስ እንዳለባቸው እና መቆጣጠር እንደሚችሉ በፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ካሉ ጋራ ተማከሩ ዕቅድም አወጡ። እነዚህ ቤተ ክርስቲያን ደርሰው የማያውቁ ሰዎች አመጣጣቻው ከተቻለ በንግግር ዓላማቸውን ማሳካት ፤ አለበለዚያ ረብሾም ሆነ በኃይል ለመንጠቅ ሙከራ ማድረግ ነበር። ውሎ አድሮ በዩቲዩብ ፣ በኢሳት ቲቪ ላይ ቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ሲያደርጉ የነበሩትን አሳዝኝ ምግባር ላየ ፤ በውኑ እነዚህ ሰዎች እምነት አላቸውን ብሎ ሊጠራጠር ግድ ይለዋል።

የሆኖ ሆኖ የሚቀጥለው የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ምርጫ ከመድረሱ በፊት የውስጥ ደንብ ላይ ስለ ምግባረ ሠናይ የተደነገገው ክፍል መሻሻል ያስፈልገዋል በማለት ፤ የመተዳዳሪያ ደንቡ (ምዕራፍ 8 አንቀጽ 51) በሚያዘው የማሻሻያ ሥነ ሥርዓት ደንብ መሠረት ሳይሆን ፤ ውስጥ ለውስጥ ራሳቸውን አዋቅረው ፤ ኮሚቴ አቋቁመው በአባ ግርማ ከበደ አቋቋሚነት ሥራቸውን ጀመሩ። ዋና ዓላማቸው ግን ይህቺን ምግባረ ሠናይ የሚያወሳው ክፍል አንቀጽ አንቀይር ብለው ሄደው ሙሉውን የውስጥ ደንብ ለመለወጥ ነበር።

...በተረታችን እንደምንለው "ውሻ በቀደደው ጅብ ይሾልካል" አይደል። ሙሉውን የውስጥ ደንብ ለመሥራት ደግሞ ጊዜ ይወስዳል ፤ ስለዚህ በተቻለ አቅም የሚቀጥለው የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ምርጫ የቤተ ክርስቲያኗ ግዢ እስኪጠናቀቅ ለሦስት ወር ይራዘም ብለው ሰበብ በመፍጠር ፤ በጣም አሳፋሪ በሆነ ዓይነት የድምፅ አሰጣጥ እንዲራዘም አድርገው የሚቀጥለውን ሤራቸውን ጀመሩ። በመጀመሪያ ምክራቸውም የካህናት ጉባኤን ለማፍረስ በገንዘብ በቀላሉ ለሚደለሉት ካህናት ደሞዛቸውን ጨምሮ ፤ እነዚህ በገንዘብ ጥቅም የተደለደሉትን ካህናት ተጠቅሞ ሌሎቹን ማባረር ነበር። በውሳኔው መሠረት ለአባ ግርማ ከበደ ፣ መምሬ አባተ ጎበና ፣ ለመምሬ ብርሃኑ ብሥራት እና መሪጌታ አለማየሁ ደሞዛቸውን ከ 400-500 ፓውንድ ከነበረው አንስተው ከአንድ ሺህ ብር በላይ ካደረጉላቸው በኋላ ፤ በስራቸው በማድረግ ላለሙለት ዓላማ መሣሪያ አድርገው ተጠቅመውባቸዋል። ያገሬ ሰው እንደሚለው <u>"ሆዱን የወደደ ማዕረጉን ይጥላል"</u> እንዲል። ይሁዳ ያስተማረውን ጌታውን እና መምህሩን በ30 ብር እንደሸጠ ፤ እነዚህም ካህናት ለማትረባ ተጨማሪ ብር ፤ የሙዳይ ምጽዋቷዋን ሣንቲም ብቻ እያዩ አርቀው ሳያስተውሉ ፤ አብረው ለዓመታት ያገለገሉ ካህናት ወንድሞቻቸውን ከቤተ ክርስቲያን አደባባይ ፣ ከአገልግሎት እንዲታገዱ ዋና መሪ በመሆን ግንባር ቀደም ሚና ተጫወቱ። በአንድ ወቅት ካህናት ከጥግ እስከጥግ ሞልተው መቆሚያ ቦታ እንዳልጠፋ ፤ በእነዚህ ለሆዳቸው ባደሩ ፣ በሙዳይ ምጽዋት ሣንቲም ፍቅር በታወሩ ካህናት መሣሪያነት አገልግሎቱ ተዳክሞ ፤ ነገር ግን በቅዱሱ ሥፍራ ላይ በየሳምንቱ የውግዘት ፣ የጥላቻ ፣ የሐሰት ክስ እና የካህናት ስንብት ደብዳቤ ማንበቢያ መድረክ ሆኖ ቆይቷል። [http://www.youtube.com/watch?v=gkCUuleM-dI&feature=mfu_in_order&list=UL](http://www.youtube.com/watch?v=gkCUuleM-dI&feature=mfu_in_order&list=UL)

እነ ሻለቃ ማሞ ለማ እና ጌታቸው በሻውረድ ከጀሌዎች ጋራ ሆነው በቀላሉ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ ካህናትን በሣንቲም ካሳወሩና ፤ የውስጥ ደንቡን የሚያውቁትን ተቆርቋሪ ካህናትን ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን ካገለሉ በኋላ ፤ እናሻሽል ብለው የጠየቁትን የምግባረ ሠናይን የሚመለከተውን አንቀጽ 30 ብቻ ሳይሆን ፤ ለእነርሱ እንዲመች አድርገው መግባት የማያስችላቸውን አንቀጾች በመለወጥ ፤ ሙሉ ሕጉን ለመለወጥ መሥራት ጀመሩ። ያ ብላሽ ፤ የማይረባ የሆነውንም ረቂቅ ፤ በድብቅ ሲሠሩ ከርመው የመጡት በቀጥታ ለማስፀደቅና ምርጫውን አካሂደው ተመራርጠው በመግባት ቤተ ክርስቲያኗን ለመቆጣጠርና ዋናው የሙዳይ

ምፅዋቱ ተጠቃሚ ለመሆን ነበር። ይሁን እንጂ እነዚህ መርዘኛ ሰዎች ያረቀቁት የውስጠ ደንብ ፤ እነዚያ ተባባሪዎቻቸው የነበሩት ካህናት ሲያዩ ፤ ቤተ ክርስቲያኗን ወደ ቦርድ አስተዳደር የሚወስድና ፤ እነሱን (ካህናቱን) ቅጥረኛ ስለሚያደርግ እንዲሁም በመጨረሻ ምንም የጥቅም ዋስትና እንደሌላቸው ሲያውቁ ፤ ልክ መጥፎ ሕልም ሲያይ እንደቆየ ሰው ነቅተው ፤ ምዕመናኑን ቤተ ክርስቲያናችሁን አድኑ እያሉ መማፀን ጀመሩ። እዚህ ላይ አንድ ነገር አስተውሉ - እነዚህ ሳንቲም አምላካቸው የሆኑ ካህናት ከእነ ሻለቃ ማሞ ለማ እና ጌታቸው በሻውረድ ጀሌዎች ጋራ ሆነው ሲያብዱ ፤ ሽማግሌዎች ደጋግመው በመሔድ እባካችሁ የምትሠሩት ትክክል አይደለም ተው ብለው ሲመክሯቸው ፤ በተለይ አባ ግርማ ያሳዩ የነበረው የንቀትና ዕብሪት ባሕሪ እስከ መቼም አይረሳም።

ምዕመናኑም ምንም እንኳን በእነዚህ ይሉኝታ በሌላቸው ፣ በጥቅም በታወሩ ካህናት ቅሬታ ቢኖራቸውም ፤ ብዙ የተደከመበትን ቤተ ክርስቲያናቸውን ለበለጠ ጅብ አናስረክብም ብለው ለማዳን ተረባረቡ። ይህ የሕዝብ ዕርዳታ ሲመጣ አሁንም የሚያስቡት ፤ የሕዝብ ድጋፍ አለን ፤ እንደገና ተመልሰን ሥልጣኑን ይዘን እንቀጥላለን ብለው ነው እንጂ ፤ ከዚህ ጉድ አወጡን ፤ ካሁን በኋላ ከእኛ በዕውቀትና በአስተሳሰብ የተሻሉ ሰዎች ይምሩት የሚል አይደለም። ሁልጊዜ የሚያስቡት እነሱ ብቻ ብልጥ ፤ ሕዝቡን በመከፋፋል ቦታውን ተቆጣጥረው ሙዳይ ምጽዋትዋ ላይ እንደ መዥገር ተጣብቀው መቆየት እስከቻሉ ድረስ መሰንበት ፤ ካልቻሉ ደግሞ አህያ እንዳለች "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" ብለው ቦታው ረብሸው ወይ ዘግተው ካላሆነም ለሌላ ኃይል አስረክበው ከመሄድ የማይመለሱ ናቸው።

የሆኖ ሆኖ በመጨረሻም ግጭቱ እየከረረ ሄዶ ፤ ሁላችሁም እንደምታውቁት 2010 ዓ.ም ላይ ጊዜውን መጨረስ የነበረበት የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ፤ በራሳቸው ፈቃድ ቆይተው ከሦስት ዓመት በኋላ በ2013 ዓ.ም ከአቅማቸው በላይ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኗን መጋቢት 10 ቀን 2005 ዓ.ም ዘግተው ፤ ሕዝቡን በትነው ሄደዋል። ቤተ ክርስቲያኗ በተዘጋጅበት ወቅት ፤ በግቢው ውስጥ የታየውም ሁኔታ የሚያስቅ ፣ የሚያሳዝንም ነበር። እነዚህ የተጣሉ ክፍሎች በተለያየ አቅጣጫ ላይ ቆመው ጸሎት ሲያደርሱ ፤ በትክክል የቤተ ክርስቲያኗን ሕግና ሥርዓት ተረድተዋል ወይ ብሎ የማይጠይቅ ሰው ያለ አይመስለኝም። ቂምና በቀል እያሰቡ የተጸለየውን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር እንደማያርግ ጌታ ራሱ ምድር ላይ በነበረበት ጊዜ አስተምሯል። ስለዚህ ያ ሁሉ በብርድ መንከራተት ትርፋ ድካምና እኔ የእገሌ ደጋፊ ወይም የእገሌ ቡድን ለማለት ካልሆነ ትርፋ ድካምና የአካባቢውን ሕዝብ መረበሽ ብቻ ነበር። ለነገሩ ረብሻውን የሚመሩት ሰዎች ለጥቅምና ለሥልጣን እንዲሁም የሳንቲም ፍቅር አስገድዷቸው ስለሆነ ምንም ነገር ቢያደርጉ አይደንቅም። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ የተዘጋችው የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያንም ፤ በታህሳስ 2006 ዓ.ም ተከፍታ አገልግሎት ጀምራለች።

## የሚቀጥለው የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ምርጫ ሂደት

ቤተ ክርስቲያኗ ከተከፈተች ጀምሮ ጊዚያዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ መደበኛው አገልግሎት ተጀምሯል። ደስ የሚለው ብዙ ምዕመናን አሁንም በጸሎተ ቅዳሴው ጊዜ ቤተ ክርስቲያኗ በመገኘት ተሳታፊ መሆናቸው ነው። በአንጻሩ ደግሞ እነ ሻለቃ ማሞ ለማ እና ጌታቸው በሻውረድ ከጀሌዎች ጋራ ሆነው አሁንም ግቢ ውስጥ ለብቻቸው ይጸልያሉ። ይሁን እንጂ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ያላቸው አማራጭ ፤ አብረው ከሌላው ምዕመናን ጋራ ውስጥ ገብቶ መጸለይ እንጂ ፤ አሁን እንደሚያደርጉት አይቀጥልም።

ቤተ ክርስቲያኗ ሥራዋን በተቀላጠፈ ሁኔታ እንድታካሂድ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ እና የንዑሳን ኮሚቴዎች ምርጫን ለማካሄድ የአስመራጭ ኮሚቴ ተሰይሟል። አሁንም ችግሩ የተመረጠው የአስመራጭ ኮሚቴ የትኛውንም የቤተ ክርስቲያኗን ሕግ (በውስጠ ደንቡ ፤ በቃለ አዋዲውም ፣ በ1992 ትረስቲ ዲድ) ያልተከተለ ፤ ወደፊትም ወደ ሌላ ችግር ሊያመራ ስለሚችል ከወዲሁ ሊታረም ይገባዋል። ይሁን እንጂ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ እና የንዑሳን ኮሚቴዎች ምርጫ የሚካሄደው በየትኛው ሕግ ነው የሚለው ከቀን ወደ ቀን አከራካሪ እየሆነ መጥቷል። ይኼ ደግሞ ምንም በማያወላውል ሁኔታ ከላይ እንደገለጽኩት በ1998 ዓ.ም (2006) አጠቃላይ የምዕመናን ጉባዔ ባጸደቀው የውስጠ ደንብ ብቻ ነው መሆን ያለበት። ይሁን እንጂ መምሬ አባተ እና መሰሎቹ የ1998 ዓ.ም (2006) ውስጠ ደንብ ችግር አስነስቷል ፣ በሽታ ነው የመሳሰሉትን በመናገርና በማደናገር ፤ በውስጠ ደንቡ ሳይሆን በቃለ አዋዲ ነው መሆን ያለበት በማለት ፤ እንደገና ምዕመናኑን መከፋፋል ጀምረዋል። ውስጠ ደንቡን ያልፈለጉበት ዋናው ምክንያት ግን ፤ እንደገና በሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አስተዳደር ውስጥ ተመልሶ ተመርጦ ገብቶ ቦታውን ለመያዝና ያቺ ሙዳየ ምጽዋትዋ ለመቀራመት ነው።

## <u>የ2006 ውስጥ ደንብ ሕጋዊ ነውን?</u>

<u>የውስጠ ደንቡ በጠቅላላው መንፈሳዊ ጉባኤ በ1998 ዓ.ም (2006) ጸድቆ አገልግሎት</u> ላይ ውሏል። ይህ ደንብ በወጣ በዓመቱ በ1999 ዓ.ም (2007) የተካሄደው የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ምርጫ በዚሁ የውስጠ ደንብ መሆኑን ሁሉ የሚያውቀው ነው። ይህ ደግሞ የዚህን ደንብ ሕጋዊነት ያረጋግጣል። ተጨማሪ ማረጋጋጫው እነ ሻለቃ ማሞ ለማ እና ጌታቸው በሻውረድ የውስጥ ደንብ ላይ ስለ ምግባረ ሠናይ የሚያወሳው አንቀጽ 30 እናሻሽላለን ብለው የፈጠሩት ትርምስ ነው። መምሬ አባተ እና መሰሎቹ ይህቺን ምክንያት ይዘው ፤ ሕጉ ችግር ስለነበረው ነው ለዚህ ሁሉ የበቃነው ብለው በሕጉ ለማማካኘት ይሞክራሉ። <u>እንዲያውም እስከዛሬ ለተፈጠሩ ችግር ዋናው ምክንያት የሕግን የበላይነትን ስለማንቀበል ፣ ሕግ እያለ የሚመስሉንን ይዘን በድምፅ ብልጫ ውሳኔ ማሳለፍ የምንፈልግ ሕዝቦች ስለሆንን ነው። ጤነኛ ጭንቅላት ያለው ሰው እንዲሁ ግልጹን ዐይቶ መፍረድ ይችላል። </u>ችግር አለበት ይሻሻል የተባለው አንቀጽ ከላይ እንደተገለፀው አንቀጽ 30 ብቻ ነው። ይህ ማለት የተቀረው ጥሩ ነው ማለት ነው። ቀደም ብዬ እንደ ገለጽኩት ግን የእነ ሻለቃ ማሞ ለማ እና የጌታቸው በሻውረድ ኮሚቴ ለእነሱ እንዲመች አድርገው በማጭበርበር ሙሉ ሕጉን ለውጦ ስለመጣ ፤ ሕጉ ችግር አለው ማለት አያስችልም። ውስጠ ደንቡን አሻሽሉ ብሎ ማንዴት የተሰጠበት ስብሰባም የለም። የሰበካ አስተዳደር ጉባኤው እንድንሠራ ፈቅዶ ነው ቢሉ ፤ የውስጠ ደንቡ ይህንን አሠራር አይፈቅድም ፤ ስለዚህ ውድቅ ነው። በመሠረቱ ሕግን ማክበር የማይፈልግ ሌባ ፣ ወንጀለኛ ፣ ቀማኛ ወይም ደግሞ የራሱ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚፈልግ ሥርዓተ አልበኛ ሰው ነው።

ሌላው የተሰጠው ምክንያት የውስጠ ደንቡን መጠቀም የማይቻልበት ደግሞ ፤ <u>በ1998 ዓ.ም (2006)</u> ጠቅላላ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ቢያጸድቀውም ፤ በወቅቱ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤው ለቻሪቲ ኮሚሽን አላስታወቀም የሚል ነው። በመሠረቱ ሕጉ ለመጽደቁ ማንም የሚክደው አይደለም። ይሁን እንጂ በወቅቱ የነበረው የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ እጅና ጓንት ሆኖ ከመጀመሪያውኑ ከእነ ሻለቃ ማሞ ለማ እና ጌታቸው በሻውረድ ጀሌዎች ጋር ፤ ይህቺን ቤተ ክርስቲያን እንዴት አድርጎ መቆጣጣር እንደሚችሉና ፤ በሥልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ መቆየት የሚያስብ ስለነበር ፤ ሆን ብሎ በወቅቱ ለቻሪቲ ኮሚሽን ባለማስገባቱ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ይጠየቅበታል እንጂ ፤ ውስጠ ደንቡ ሕጋዊ አይደለም ብሎ መናገር ሌላውን ሰው አእምሮ የለሽ ማድረግ ነው። ረጅም ጊዜ ለመቆየት ፍላጎቱ እንዳለቸው አንዱ ማስረጃ ከ 11 ዓመታት በላይ በሰበካ

አስተዳደር ጉባኤ ምክትል ሊቀ መንበርነት የመራው ታዬ ኃይሉ በ 31 July 2011 በቤተ ክርስቲያኒቷ በተካሄደው የሰ/አ/ጉባዔው ስብሰባ ላይ ፤ ብድግ ብሎ ተነስቶ በድጋሚ ከመረጣችሁኝ ወደፊትም ለመሥራት ፈቃደኛ ነኝ ብሎ ሲናገር መስማቱ ይህ ሰው ምን ያህል የሥልጣን ጥማት ወይም ደግሞ ሌላ የሚቀርበት ጥቅም እንዳለ የሚያመለክት ነው። እንደውም ቤተ ክርስቲያን የይቅርታ አደባባይ ስለሆነች ክስ አትመሠርትም እንጂ ፤ እነዚህ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አባላት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣትና በገንዘብ ማባከን ሊከሰሱ ይገባ ነበር። ለነገሩ ግን አስፈላጊ ከሆነ በግል ደረጃም ቢሆን ሊከሰሱ ይችላሉ።

የቻሪቲ ኮሚሽን የተመዘገብንበት ዋናው ምክንያት ታክስ እንዳንከፍል ነው እንጂ እነሱ እንዲያስተዳድሩን አይደለም። በ1992 የተመዘገብንበት ዶክዩመንት እስከዛሬ ተጠቅመንበት ራሱ አናውቅም። የቻሪቲ ኮሚሽን ዲድስ ስለ ቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር እና ንዑሳን ኮሚቴዎች አመሠራረት አይገልጽም። አዲስ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ሲመረጥም ፤ የአዲስ ተመራጮቹ ስም ዝርዝር ሲላክ ፤ እንደ ተመዘገባችሁበት ሕግ ለምን አልተመራረጣችሁም ብለውም አያውቁም። የ1998 ዓ.ም (2006) ያወጣችሁት ደንብ ቀድሞ ስላልደረሰን በሱ መመራረጥ አትችሉም ሊሉንም መብት የላቸውም። <u>ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያናችን በዚህ ሀገር በሕግ የተቋቋመችና በቻሪቲ ኮሚሽንም church/charity በመባል በድርብ የምትታወቅና ለመንፈሳዊ አገልግሎት በውስጠ ደንቧ ፤ ለምግባረ ሠናይ ለገንዘብና ንብረት ቁጥጥር በቻሪቲ ዲድስ የምትመራ ናት። ስለዚህ ማንኛውም አካል ቻሪቲ ኮሚሽንን ጨምሮ በእምነት ተቋምነቷ ላይ በምታደርገው ምርጫ ጣልቃ ሊገባ አይችልም።</u>

<u>የውስጥ ደንቡ ይሻር ቢባል እንኳ ፤ አሁንም መሻር የሚችለው አጠቃላይ መንፈሳዊ ጉባኤ እንጂ መምሬ አባተ እና መሰሎቹ ብቻቸውን አይደለም። እንደ አፍሪቃ መሪዎች እኛ እናውቅልሃለን ማለት ካልሆነ በስተቀር።</u> አለበለዚያ ግን አሁን ሁሉን ነገር ተቆጣጣረናል ፤ እንደፈለግነው እንመርጣለን ብለው ሕጋዊ ያልሆነ ሥራ ከተሠራ ፤ ከእነ ሻለቃ ማሞ ለማ እና ጌታቸው በሻውረድ ጀሌዎች ጋር ምንም ልዩነት የለም ማለት ነው። ቀጣዩ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ምርጫ አለ <u>ውስጥ ደንቡ ፤</u> ነገር ግን በቃለ አዋዲው እና በ1992 በቻሪቲ በተመዘገብንበት ሕግ ብቻ ከሆነ ፤ ውሎ አድሮ ችግር የሚያመጣ ነው። ሌላው ቢቀር ሊለውጡት የሞከሩት እነ ሻለቃ ማሞ ለማ እና ጌታቸው በሻውረድ እንዲሁም ጀሌዎቻቸው ምርጫው ሕጋዊ አይደለም በማለት ለክስ ሊጠቀሙበት ይችላሉ የትም ባያደርሳቸውም።

<u>ለምንድን ነው መምሬ አባተ እና መሰሎቹ የ2006 ውስጥ ደንብን የሚጠሉት?</u>

ምርጫው በቃለ አዋዲው እና በ1992 በቻሪቲ ዲድስ ከሆነ ፤ የቤተ ክርስቲያኒቷ አስተዳዳሪ የሚሾመው በሀገረ ስብከቱ ወይም ከኢትዮጵያ ሊሆን ይችላል። ከኢትዮጵያ አስተዳዳሪ ተሹሞ ቢላክ ፤ ከወጪው ጫና ባሻገር ብዙ ክፍፍልን የሚያስነሳና ቤተ ክርስቲያኗን ወደ ከፍተኛ ችግር ውስጥ የሚከት ነው። ምርጫው በቃለ አዋዲው ነው ካልን ደግሞ ፤ አብሮ የሚመጣውንም መቀበል ግዴታ አለብን። በቃለ አዋዲውና በውስጠ ደንቡ መካከል ብዙ ልዩነት የሌለ ሲሆን ፤ የውስጥ ደንቡ ግን የውስጥ አስተዳደራችንን በግልጽ ያሳያል።

ምርጫው በውስጠ ደንቡ ከሆነ ግን አስተዳዳሪው የሚመረጠው በአንቀጽ 35 መሠረት በቤተ ክርስቲያኗ ምዕመናን ስለሆነ ፤ ይህን ሁሉ ትርምስ በመፈጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉትን እንደ አባ ግርማ ከበደ ፣ መምሬ አባተ ጎበና ፣ እና መሪጌታ አለማየሁ የመሰሉትን ለምርጫ እንዳይቀርቡ ይከለክላቸዋል። ምክኒያቱም

ለአስተዳዳሪነት ብቻ ሳይሆን ፤ ለሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ምርጫ ላይ ለመሳተፍ ራሱ ብቁ አይደሉም። ለምን ብቁ እንዳልሆኑ የካህናት መመዘኛውን አንቀጽ 9 ማየት ነው። ነገር ግን ለምዕመናን በመድረክ ላይ ሲናገሩ በቶሎ አስረክበው ከኃላፊነት መገለገል እንደሚፈልጉ አድርገው ነው። ምዕመናን ደግሞ እውነትም እነዚህ ሰዎች ደክመዋል ብለው የውስጥ ተንኮላቸውን ሳያውቁ ያዝኑላቸዋል። ምዕመናን ማወቅ ያለባቸው እነዚህ በጥቅም የታወሩ ካህናት ፤ የሚናገሩትና የሚያደርጉት የተለያየ መሆኑን መገንዘብና መጠንቀቅ ያስፈልጋቸዋል። እነዚህ ካህናት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በአንድ በኩል ካህናቱ መጥተው በአንድነት አብረን ማገልገል እንፈልጋለን እያሉ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በውጭ ያሉ ካህናት መጀመሪያ እንዲመጡ ከተፈለገ ፤ በጠቅላላ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የፀደቀውን የውስጠ ደንብ መከበር አለበት ብለው የጠየቁትን ጥያቄ አንቀበልም በማለት ዕርቁ እንዳይፈፀም የውስጥ ተንኮል ይሠራሉ። የዚህ ዋና ዓላማው ደግሞ የውስጠ ደንብ አንቀበልም በማለት እነዚህ አለአግባብ የተባረሩ ካህናት ተመልሰው እንዳይመጡ ማድረግና ፤ ሌላ የሚረከብ ካህን ስለማይኖር እነዚሁ በጥባጭ ካህናት ይቀጥላሉ ማለት ነው። በተጨማሪም ሊመረጡ የሚችሉ በቂ ካህናት በቤተ ክርስቲያኗን ስለሌሉ ፤ ከሀገረ ስብከቱ ወይም የእነሱ ቢጤዎች የሆኑ ሌሎች ካህናትን ከሌላ ቤተ ክርስቲያን በማምጣት እንዲመረጡ ከማድረግ አይቆጠቡም። ከውጭ ደግሞ የሚመጡት የራሳቸው ሌላ ዓላማ ይዘው ስለሚመጡ ቤተ ክርስቲያኗን ወደ ሌላ ከፍተኛ ችግር ይዳርጋታል ማለት ነው።

## አንቀጽ 9
## የተመራጭ አባላት መመዘኛ

### 1. የካህናት ተመራጮች መመዘኛ

ሀ) በቤተክርስቲያኑ የካህናት ጉባኤ መዝገብ የተመዘገቡና የካህናት ጉባኤዉ በሚያወጣዉ የአገልግሎት መር ሐ ግብር መሠረት ቢያንስ ለአንድ ዓመት ተገቢዉን መንፈሳዊ አገልግሎት የሰጡ።

ለ) ሥጋዊ ጥቅም፤ የሥልጣን ሽሚያ፤ ዘረኝነትና ጎጠኝነት አስተሳሰባቸውን ያዛባዋል ተብለው የማይጠረጠሩ።

ሐ) ከተንኮልና ከአድማ የራቁ፤ የቤተክርስቲያንን ሥርዓትና ሥነምግባር ጠብቀዉ የሚያስጠብቁና አክብረዉ የሚያስከብሩ።

መ) ለቤተክርስቲያን አገልግሎት፤ ለስብከተወንጌልና ለጸሎት የሚተጉ።

ሠ) የገንዘብ ጉድለት ያልተገኘባቸው በወንጀል ተከሰው በጉባኤ ያልተወሰነባቸው ወይም በማናቸውም ሁኔታ መብታቸው በሕግ ያልተገደበባቸው።

ረ) በማንኛዉም የፖለቲካ ፓርቲ ዉስጥ የአመራር አባል ያልሆኑ።

ሰ) ለምግረ ሠናይ ኮሚቴ የሚመረጡና በሰበካዉ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ በገንዘብ ሰነድ ፈራሚነት የሚ መደቡ አባላት በቤተክርስቲያኑ ውስጥ በደመወዝ ወይም በአበል አገልጋይ (ተቀጣሪ) ያልሆኑና ቁሳዊ ጥቅ ም የሌላቸው፤

ሸ) በብሪታንያ የመኖሪያ ፍቃድ ያላቸዉ እና እድሜያቸዉ ከ25 ዓመት በላይ የሆኑ ካህናት ይሆናሉ።

ቀ) የቤተክርስቲያኑን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብና አቋም አክብረው ማስከበር የሚችሉ ካህናት እየተጠቆሙ ይመረጣሉ።

በጥቂቱ ከላይ በቢጫ የደመቁት ዐረፍተ ነገሮች ከብዙ በጥቂቱ የፈፀሚቸው አሳፋሪ ድርጊቶች ናቸው።

## በጥቂቱ የታመነ በብዙ ይሾማል (ማቴ 25 ፤14-31)

ይህን ቃል የተናገረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ አባባል በመንፈሳዊም ይሁን በሥጋዊ ቦታ ላይ ይሠራል። በቤተ ክርስቲያናችን በአለፉት ዓመታት ተራ በሆነ ልክስክስነት ብዙ ገንዘብ እንዴት ይዘረፍ እንደነበር የወጣውን ጽሑፍ ማንበብ ነው። http://ethioview.com/images/london/corruptionAUG2011.pdf

በተለምዶ አሠራር እንዲህ ዓይነት ክስ ሲሰማ ፤ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ሁኔታውን አጣርቶ የሰውን ጥርጣሬ ለማብከን ፤ ለምዕመናኑ ሪፖርት ማቅረብ ይጠበቅበታል። ነገር ግን አባ ግርማ ከበደ ይህን ሁሉ እያዩ በወቅቱ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አልሰማ ቢል ፤ ለሚመለከታቸው ንዑሳን ኮሚቴ ማቅረብና ችግሩን መፍታት ነበረባቸው። ነገር ግን የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አባላት ፣ እነ ሻለቃ ማሞ ለማ እና ጌታቸው በሻውረድ እንዲሁም ጥቂቶቹ በጥቅም የተገዙት ካህናት ሆን ብለው ኮሚቴዎቹን ስላፈረሱ ለዝርፊያው ዕድሉን ከፍቶላቸዋል። ቢሆንም አባ ግርማ ከበደ በጥቅም ከእንዚህ ሰዎች ጋር ባይያያዙ ኖሮ ወይም ከጉዳይ ነፃ ቢሆኑ ኖሮ ፤ ጉዳዩን ወደ ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ በማምጣት ምዕመናን እንዲያውቁት ማድረግና ምዝበራው እንዲቆም የማድረግ ትልቅ ኃላፊነት ነበረባቸው። ስለዚህ አባ ግርማ ከበደ ይህና ሌሎችም የፈጸሚቸው ስህተቶች ፤ ይህቺን ቤተ ክርስቲያን ለማስተዳደር ሳይሆን በንዑስ ኮሚቴ ደረጃ ገብተው እንዲሠሩ ማድረግ ፤ በቦታው ላይ ሰው እንደሌለና ፤ እንደገና እኝህን ሰው በቦታው ላይ ድጋሚ እንዲቀልዱበት ዕድሉን መስጠት ነው።

እንዲሁም ከአባ ግርማ በማይተናናስ ሁኔታ ፤ መምሬ አባተ ጎበና ፤ በቤተ ክርስቲያኗ መድረክ ላይ ሌሎች ካህናትን በሳንቲም ፍቅር ታውሮ ሲዘልፍና ሲሳደብ የነበረ ፤ ውስጡ በጥላቻ የተበተበ ፣ ቤተ ክርስቲያናችን ከመጣበት ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ለካህናት ጉባኤ መፍረስና ፣ የአዞ ዕንባ እያነባ ለምዕመናን መከፋፋል ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገ ግለሰብ ነው። በተጨማሪም ለዚህ ሁሉ ትርምስና ግጭት ከሚጠየቁት የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አባላት አንዱ ሲሆን ፤ ወደፊት ኮሚቴ ተቋቁሞ የተፈጠረው ችግር እስኪጣራ በሕጉ መሠራት እሱም ሆነ ከእሱ ጋራ ሲሠሩ የነበሩት ቤተ ክርስቲያኗን ዘግተው የጠፉትን የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አባላት ፤ ምንም ኮሚቴ ውስጥ ገብተው መሥራት አይችሉም። በተለይ ደግሞ መምሬ አባተ ከላይ የተመለከቱት ድኅረ ገጽ ላይ ለወጡት ክሶች በወጡ ሰሞን ፤ በግልጽ በማስረዳትና ራሳቸውን ነፃ ከማውጣት ይልቅ ፤ እባካችሁ ከቤተ ክርስቲያኗ ድኅረ ገጽ ውጪ ሌላ ድኅረ ገጽ ላይ የሚወጡን ሌሎች ጽሑፎች አታንብቡ ብሎ ፤ ቤተ ክርስቲያኗ መድረክ ላይ ሲናገር መስማት ፤ ምን ያህል የሙዳየ ምጽዋቱ ብር አስተሳሰቡን እንዳበላሸው ወይም በክሱ እንዳፈረ መረዳት አያዳግትም። አቅሙ ቢኖረው እንግዲህ ጉዳቸውን የሚያጋልጡትን ማንኛውም ዐይነት የሚዲያ ተቋሞች ከመዝጋት የማይመለስና ፤ በጸሐፊዎች ላይስ ጉዳት ለማድረስ ምን ያግደዋል። በራሱ የሚተማመን ሰው ግን ምንም ቢጻፍበት ከቁም ነገር ሳይቆጥረው ስቆ ይረሳዋል። ነገር ግን ወንጀልን የፈጸመ ሰው ፤ ሌላ ተጨማሪ መጋለጥ ከመድረሱ በፊት ፤ ከሳሹን ዝም ለማድረግ በሚቻለው ሁሉ ይጥራል። ደግነቱ ያለንበት ሀገር ከዚህ ዐይነቱ ብቀላ ይከላከላል።

## ባለፉት ዓመታት የተፈጠረውን ችግርና የገንዘብ ምዝበራ አስመልክቶ አጣሪ ኮሚቴ ስለማቋቋም

የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተች 40 ዓመታት ያስቆጠረች ሲሆን ከእነዚህ ዓመታት ውስጥ በተለይ ያለፉትን 22 ዓመታት አለምንም ግጭት የታለፈበት ዓመት የለም። ታዲያ በእነዚህ ዓመታት ችግር ሲፈጠር መንስዔው ምን እንደሆነ ፤ የግጭቱ ፈጣሪዎች እነማን እንደሆኑ ፣ ወደፊት እንዳይደገም የተወሰደውን እርምጃ አካቶ የያዘ ሪፖርት እንዲያቀርብ ኮሚቴ ተቋቁሞ አያውቅም። በ2004 የመምሬ ብርሃኑ ብሥራትን ጉዳይ እንዲያጣራ የተቋቋመው ኮሚቴም በግለሰቦች የተጻፉትን ጽሑፎች እውነተኝነታቸውን እንዲያጣራ ነበር እንጂ ከሥር መሠረቱ ራሳቸው መርምረው እንዲሠሩ አልነበረም። ይሁን እንጂ የተጻፉት ጽሑፎች በግልጽ መምሬ ብርሃኑ ብሥራት የፈጸሟቸውን ስህተቶች ስላሰፈሩ ትክክለኛነታቸውን አረጋግጠዋል።

አሁንም ከዚህ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ምርጫ በኋላ አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ፤ የተፈፀሙትን ስህተቶች ፣ የስህተቱ ፈጣሪዎች እነማን እንደሆኑ ፣ የተጣሰውን የውስጠ ደንብ አስመልክቶ ፤ የገንዘብ ምዝበራውን ፣ ያሉትን ንብረቶች በእርግጥ መኖራቸውን ፣ ቀደም ብሎ የተጻፉትን ጽሑፎች እንደ መንደርደሪያ በማድረግ ፣ እውነት መሆናቸውን ወይም ስም ማጥፋትም ከሆነ አጣርቶ ሪፖርት እንዲያቀርብ ያስፈልጋል። ከዚያም ሊወሰድ የሚያስፈልገውን ውሳኔ በሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አማካኝነት ለጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ በማቅረብ ፤ ወደፊት በአለፉት ዓመታት እንደተፈጠረው ዓይነት ችግር እንዳይደገም ውሳኔ ማሳለፍ ይኖርበታል። ይህ ጊዜ ያልገደበው ችግር ካሁን በኋላ ሊቆም ይገባዋል።

## ማጠቃለያ

ከ40 ዓመት በላይ ዕድሜ ያላትን የለንደን ደብረ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ከምሥረታዋ ጀምሮ እስካሁን የተጓዘችበትን ጎዳና አጠር ባላ መልኩ ለማሳየት ሞክሬአለሁ። በእነዚህ ዓመታት ተደጋጋሞ የታየው የራስን ጥቅም ለሟሟላት ሲባል ፤ የብዙኃኑን ምዕመናን ፍላጎት ከምንም ባላመቁጠር ፤ ሕግን በመጣስ በተፈፀሙ ድርጊቶች ፤ የአገልግሎት መቋረጥ አንሶ ብዙ ካህናትና ምዕመናን ከደከሙበትና ከለፉበት ቤተ ክርስቲያናቸው ርቀዋል። ብዙ ጊዜ እንዳየሁት ይህች ቤተ ክርስቲያን ተደጋግሞ ችግር ውስጥ ልትወድቅ የቻለችው ፤ አንዳንዶች በይሉኝታ ወይም በጥቅም የተገናኙ ፤ አንዳንድ በተንኮል እና በክፋት የተመሉ ሰዎች ስሕተት ሲያደርጉና ቤተ ክርስቲያኗን ሲያምሱ እንደመምከርና እንደማረም ፤ በቤተሰብነት ወይም በጓደኝነት ብቻ እየደገፉ ፤ እገሌ እንዲህ ነው አሉ .... እገሌ ደግሞ እንደዚያ እያሉ ነገር በማራገብ ለብዙዎች መሰናከል ምክንያት ሆነዋል። በአቅራቢያችን ያሉት ለብዙ ዓመት የምናውቃቸው ፤ ሰው የነገራቸውን ብቻ ሰምተው ፤ ስለሁኔታው በደንብ አጣርቶ ፤ ለምን እንዲህ ሆነ ከማለት ይልቅ ፤ በበለጠ ወሬውን አጋነው ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ እንዲወጣ ያደረጉን ታዝበናል።

እዚህ በሰለጠነው ሀገር ስንኖር ትምህርት ቤት ሳንሄድ ብዙ ምንማራቸው ነገሮች አሉ። የምርጫ ጊዜ ሲፈፀም ጊዜውን አክብሮ ከሥልጣን መውረድ እንጂ ፤ እንደ አፍሪቃ መሪዎች አሻፈረኝ ብሎ ለሥልጣን መጋደል ፤ በተለይ ለአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ኮሚቴ አባል ለመሆን ድፍን ሀገር ማመስ ትዝብት ያስከትላል። ወሬ ሰምቶ ብቻ ወሬውን ከማቀጣጣል በፊት እውነታውን መገንዘብና ነገሮችን አመዛዝኖ ፤ እውነት ላይ ተመሥርቶ ሰላምን ማውረድ እንጂ ፤ አድመኝነትን ማስወገድ ከአንድ ሥርዓት ካለው ሕዝብ የሚጠበቅ ባህርይ ነው። እዚህ ላይ አንድ ምሳሌ መስጠት እፈልጋለው። በ2011 ለንደን በተረበሸ ጊዜ ፤

በዚያ ዝርፊያ መሐከል አንድ ቤተሰብ ልጃቸውን ከሚዘርፉት መካካል በቴሌቪዥን ላይ ዐይተው ፤ ለፖሊስ ሪፖርት እንድታደርግና አስፈላጊውን ቅጣት እንድትቀበል አድርገዋል። ይህ የሚያመለክተው ፤ ምንም አንድን ሰው ብንዛመደው እና ብንቀርበው ፤ ከእውነቱ ሲወጣ ግን ልናርመው እና ልናስተካክለው ሃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን ሰብአዊ ግዴታ አለብን። በተጨማሪም በመንደር ተመካክሮ እንዴት አድርጐ ስብሰባ እንደሚረበሽ አቀነባብሮ ከመምጣት ፤ በእልህና በጡንቻ ማሰብን ትቶ ፤ በግልጽ በመነጋገር ፤ በመደማመጥ ችግሮችን መፍታት ፤ አንድ ጤነኛ ከሆነ ማሰብ ከሚችል ሰው የሚጠበቅ ተፈጥሮአዊ ስጦታ ነው። ይህንንም ልምዳችን ልናደርገው ይገባል። በተለይ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የምንሠራው በእውነትና በቅንነት ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል።

አንድ ሰው ቃላቶችን አጣፍጦ ስለተናገረ ብቻ ልናምነው አይገባም። ነገር ግን የሰውየው ውስጣዊ መልእክት መረዳት ያስፈልጋል። ለምሳሌ አሁን ቤተ ክርስቲያኗ ከተከፈተች ወዲህ ብዙ ምዕመናን ከዚህ በፊት አለ አግባብ የተባረሩት ካህናት መጥተው ከአሁን በኋላ በአንድነት አገግሎት እንዲቀጥል ይፈልጋሉ። ይህ እንዲሆንም ሽማግሌዎች ለማስታረቅ ሞክረው ነበር ግን ለጊዜው ብዙ ውጤት አላመጣም። በውጭ ያሉት ካህናት እነዚህ በጥቂት ገንዘብ ተደልልው ያጨማለቁት የተበላሸ ነገር ውስጥ ዘለው መግባት አይፈልጉም ምንነታቸውን በደንብ ስለሚያውቁ። ካህናቱ ወደ ቤተ ክርስቲያኗ መጥተው መሳተፍ የሚጀምሩት ከዚህ በታች የተገለጹት ሲሟሉ ብቻ ነው።

1ኛ/ ይህቺን ቤተ ክርስቲያን እንደ ቀድሞው በደመቀ ሁኔታ ለማገልገል የመጀመሪያው ትልቁ ነጥብ የ1998 ዓ.ም (2006) ምዕመናኑ ያጸደቁት የውስጥ ደንብ ለቀጣዩ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ምርጫ ጠቀሜታ ላይ እንዲውልና ፤ ወደ ፊት መሻሻል ወይም መሰረዝም ካለበት ፤ የሚመረጠው የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ችግር ካለ ፤ ችግሩን አስጠንቶ የውስጥ መተዳደሪያ ደንቡ ምዕራፍ 8 አንቀጽ 51 ቁጥር 1 እና 2 በሚያዘው መሠረት እንጂ ፤ ጥቂት ካህናት ለእነርሱ ለሚፈልጉት ዓላማ ስላልተመቻቸው ብቻ ሽረው በሚፈልጉት መንገድ ብቻ ማስኬድ አይችሉም። አለበለዚያ እንዲህ ዐይነት ዐይን ያወጣ አሠራር ፣ ሕዝብ ያፀደቀውን የውስጥ ደንብ በገዛ ሥልጣን ሽሮ እንደፈለጉ መጓዝ የሚያስከትለው ጠንቅ ቀላል አይደለም ፤ ወደፊትም ያስወቅሳል። እንደ መምሬ አባተ ጎበና ያለ በላሰለሰ አንደበትና በአዞ ዕንባ ሕዝብን የሚሸነግል ፤ ሌሎች የተሻለ ካህናት ከመጡ ቦታዬን ያሳጡኛል ፤ እንዲሁም የሙዳይ ምጽዋቱን ሣንቲም ሊካፈሉኝ ወይም ሊያስቀሩብኝ ይችላሉ በማለት ፤ ሌሎች ካህናት ወደ ቤተ ክርስቲያኗ እንዳይመጡ አሁንም ተንኮል መሥራቱን አላቆመም። በተረታችን እንደምንለው "እንዳያማህ ጥራው ፣ እንዳይበላ ግፋው" እንደሚባለው ነው።

2ኛ/ በመጀመሪያው ነጥብ ከተስማሙ ፤ በቀጥታ መደረግ ያለበት ለሁሉም ቀደምት አገልጋይ ካህናት ጥሪ ተደርጎ ዕርቀ ሰላም አውርዶ በቀጥታ የካህናት ጉባኤን መመሥረት ነው። በውስጠ ደንቡ መሠረት ለምርጫ የሚቀርቡትን ካህናት የሚወክለው ይህ ጉባኤ ነውና። አለበለዚያ አሁን ሊመረጡ የሚችሉት እነዚሁ ቦታውን ሲያምሱ የነበሩ ካህናት ይሆኑና ችግሩ በቀጣይነት እየተባባሰ ይሄዳል።

ስለዚህ ምዕመናን ይህን ያለውን ሁኔታ በመረዳት ፤ በውስጥ ካሉት ካህናት ጋር በግልጽ በመነጋገር የተበላሸው አሠራር አስተካክሎ ፤ ሁሉም ካህናት ወደ ቤተ ክርስቲያኗ እንዲመጡ አድርጎ እንደቀደመው መንፈሳዊ አገልግሎቱ እንዳማረ እንዲቀጥልና ፤ ቤተ ክርስቲያኗን እየበጠበጠ ያለውን የሰይጣን ኃይል ማሳፈር ይኖርባቸዋል። አንዳንዶች ቤተ ክርስቲያኗ መከፈቷን እንጂ ስላለው ሁኔታ ማወቅም የማይፈልጉ

አሉ። ሌላው ቢቀር ቤተ ክርስቲያናችን ተከፍታለች ፤ ይሄ ጽሑፍ ለምን መጻፍ አስፈለገው ብለው የሚተቹ ፤ የዛሬውን ብቻ የሚያስቡና ስለነገው ዘላቂ መፍትሔ የማይጨነቁ ይኖራሉ። ይሄ ሁሉ ትግል ተካሂዶ መልሶ እነዚያኑ ሰዎች አስተዳደር ላይ ማስቀመጥ ፤ በሀገሩ ላይ ሰው እንደሌለና ፤ የመራጩን ሕዝብ የአእምሮ ጤንነት የሚያጠያይቅ ይሆናል። እንግዲህ እንደተባለው እሳትና ውኃ አቅርቤልሃለው ፤ እጅህን ወደ ወደድከው ክተት ነው። ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ!!

በሚቀጥለው ጊዜ ምርጫው በምን ዓይነት ሁኔታ እንደካሄደ ፣ ማን እንደተመረጠ ፣ የተመረጡት መለኪያቸው ምን እንደ ነበር ፣ እነማን አብረዋቸው ሠሩ ፤ የመሳሰሉትን ያካተተ ተከታይ ጽሑፍ አቀርባለው።

እግዚአብሔር አምላክ ቤተ ክርስቲያናችንና ሀገራችንን ይባርክ።

በእደ ማርያም እጅጉ ረታ
ሰኔ 15 ቀን 2006